

❧41-1☙

# የራሳችን የሆነ አቋም እንዲኖረን

በአጼ ኃይለ ሥላሴ ዘመን መንግሥት በተለያየ ጊዜ ጸሎት ቤቶቻችን በመንግሥት ትዕዛዝ ተዘግተው ስለነበረ፥ የምንሰበሰበው በድብቅ ነበር። አንድ ዕሁድ፥ ከአራት መቶ የማያንሱ ምዕመኖቻችን በአምልኮት ላይ እንዳሉ በፖሊስ ታፍሰው ታሰሩ። አንዳንዶቻችን የእነርሱ እጣ ያልደረሰን እነርሱን ለማስፈታት ብንሯሯጥም አልሆነልንም። በመጨረሻም ፍርድ ቤት አቀረቡአቸው። የፍርድ ቤቱ ዳኛ ሁለት ምርጫ ሰጧቸው። ይኸውም፥ አንደኛ “በመሰብሰቤ አጥፍቻለሁ” ካሉ የተወሰነ ገንዘብ ከፍለው መውጣት እንደሚችሉ፤ ሁለተኛ “አላጠፋሁም” ካሉ ግን ስድስት ወር የሚፈረድባቸው መሆኑ ተነገራቸው። በዚህ ወቅት የብዙዎቹ እምነት ተፈተነ። ስድስት ወር ወህኒ ቤት ቢቆዩ የሚደርስባቸውን ጉዳት መተመን ነበረባቸው። “ስድስት ወር መታሠር አልፈልግም፤ ብዙ ዋጋ ያስከፍለኛል” ያሉ አንዳንዶቹ ጥፋት እንደሌለባቸው ሕሊናቸው ቢመሰክርላቸውም ከእስር ለማምለጥ ብቻ “ጥፋተኛ ነኝ” እያሉ የተወሰነባቸውን ገንዘብ እየከፍሉ ከመታሠር አመለጡ። ከእስር ቤት ያምልጡ እንጂ ከህሊና ጸጸት አያመልጡም። ይህን ያልነው በእነርሱ ላይ ለመፍረድ ሳይሆን እውነቱን ለመጠቆም ያህል ብቻ ነው። ሌሎች ደግሞ “ጌታዬን ማምለኬ ጥፋት አይደለም፤ ከእስራት ለማምለጥ ስል ብቻ ጥፋተኛ ነኝ ብዬ ነጻ ብወጣ ሕሊናዬ አይቀበለውም፤ በዚህም ጌታዬ የከዳሁ ስለሚመስለኝ ፍጹም አላደርገውም” ያሉ ስድስት ወር ተፈርዶባቸው ጸጉራቸውን እየተላጩ ከርቸሌ ገቡ። የስድስት ወር ወህኒ ቤት ዘመናቸውን በማልቀስ፣ በማጉረምረምና በመጸጸት ሳይሆን በደስታ እንዳስለፉት አንዳንዶቻችን ምስክሮች ነን። እንዲያውም ብዙ ነፍሳትን ከወህኒ ቤት ወደ ጌታ አመጡ።

## “መምረጥ” መብታችን ነው

እግዚአብሔር ሰውን መሠረታዊ የሆነ “ነጻነት” ሰጥቶ ፈጠረው። ያም የመምረጥ (የመፍቀድ) ነጻነት ነው። ይሄ “የመፍቀድ” ወይንም “የመምረጥ” ነጻነት ከእግዚአብሔር የተሰጠው ሰብአዊ መብቱ ስለሆነ  ማንም መጣስ አይችልም። ራሱ እግዚአብሄርም ለሰው ፈቃድ ተገዢ ነው። ሰይጣንም ቢሆን ሰውን ከመስመር እንዲወጣ ያባብለዋል እንጂ (ዘፍጥረት 3፥4) “የመፍቀድ” ነጻነቱን ገፍፎ በማስገደድ በሕይወቱ ላይ አንድም ነገር የማድረግ ኃይልና ችሎታ የለውም። ሰው በኃጢአት ወይንም በቅድስና ለመኖር ምርጫው የራሱ ነው (ኢሳያስ 1፥19-20)። እግዚአብሔርም ምርጫውን ወይንም “ፈቃዱን” ያከብራል እንጂ አያስገድደውም። ለዚህ ነው ደህንነት እንደ ውሃ ጠምቶት ልቡ በጥያቄ ተሞልቶ ወደ ክርስቶስ የቀረበውን ሀብታም ወጣት በሃብቱ ምክንያት ከደህንነት ሲሸሽ እያየው በማስገደድ ወደ እውነት ያለመለሰው (ሉቃ 18፥18-30)። ለዚያም ሃብታም ወጣት ኢየሱስ ቢመርጥለት ኖሮ፥ መጀመሪያ የሰጠውን “የመምረጥ ነጻነት” መተላለፍ በሆነ ነበር። ሰው የራሱ ውሳኔ የራሱ ምርጫ እንዲኖረው ሆኖ ከተፈጠረ ታዲያ ለምን ይሆን ብዙዎቻችን “የግል የሆነ አቋም” ሳይኖረን “ከሚነፍሰው ጋር የምንነፍሰው?” ከሚፈሰው ጋር የምንፈሰው?”

## “ልዩ” ሆኖ መገኘት ደካማነት አይደለም

ኢየሱስ “መስሎ የማደር” ጠባይ አልነበረውም። ከሚፈሰው ጋር አልፈሰሰም። ከሚወርደው ጋር አልወረደም። ነገር ግን ጠንካራ የሆነ የራሱ የሆነ አቋም ነበረው። ሕብረተሰቡ ቢቀበለውም ባይቀበለውም ግድ አለነበረውም። መስሎና ተስማምቶ መኖር ተቀባይነት የሚያስጥ መሆኑን ቢያውቅም ያንን ዓይነት ምርጫ አልመረጠም። ሁልጊዜ ልዩ (unique) ነበር።

- በታላቅ ከተማ መወለድ ሲችል ትንሿን ቤተልሄምን መረጠ
- በቤተ መንግሥት መወለድ ሲገባው በግርግም ተወለደ
- በታላላቆች ፈንታ የበግ እረኞች የመወለዱን የምሥራች እንዲያውጁለት መረጠ
- ደቀ መዛሙርቱ እንዲሆኑ ተራ ሰዎችን መለመለ

ሁሉ ነገር ሊኖረው ሲችል ድህነትን ተቀበለ፤ “የእኔ ነው” ብሎ የሚለው ምንም ነገር አልነበረውም። ሰዎች የሚያሳዩት ውጫዊ የሆነ ግርግርና ሽር ጉድ እምብዛም አይጥመውም። በአፍ ብቻ የሚወራ ቅድስና አይጣፍጠውም። ሰዎችን ደስ ለማሰኘት ብቻ ሲል ከእምነቱ ውጪ የሚኖር፥ አቋም የሌለው ሰው ደስ አያሰኘውም።

በዓለም ሁለት ዓይነት ሰዎች አሉ። አንደኛው፥ የአካባቢን ሁኔታ የሚፈጥሩ የታሪክ ሰዎች ለአካባቢው መልክና ቅርጽ የሚያወጡ ሲሆኑ፥ ሁለተኛው፥ አካባቢው የሚፈጥራቸው ታሪክ የወለዳቸው የራሳቸው የሆነ መልክና ቅርጽ የሌላቸው የአካባቢውን መልክና ቅርጽ የያዙ ናቸው። ለመሆኑ እኛ ከየትኛው ክፍል ነን? አካባቢውን እኛ እንቀርጻለን ወይንስ አካባቢው እኛን ይቀርጸናል? ይህን ዓለም እንመስላለን ወይንስ የራሳችን አቋም አለን (ሮሜ 12፥2)? ባለታሪክ የነበሩና ዓለም ያደነቃቸው ትላልቅ ሰዎች የራሳቸው የሆነ አቋም የነበራቸው እንጂ ከሁሉም ጋር ተስማምቶ የመኖር (conformity) ጠባይ የሚያጠቃቸው አልነበሩም። ኤመርሰን የተባለው ጸሀፊ “የራስህን ዓለም መሥርት፤ በሌላው ሰው ላይ መቅናት ድንቁርና ነው፤ ሌላውን ሰው መኮረጅ ራስን በገዛ እጅ መግደል ነው” በማለት እያንዳንዱ ሰው የግል የሆነ አቋም እንዲኖረው ይመክራል።

## “ግላዊነት” መጥፎ ይሆን?

እርግጥ ነው “ግላዊነት” (individualism) የራሱን የሆነ ድካም አለው። “ግላዊነት” የሚያጠቃቸው ሰዎች በራሳቸው ላይ ከሚገባው በላይ ትኩረት ስለሚሰጡ እነርሱ ከሚያስቡት የበለጠ ሌላ ሰው ማሰብና ማድረግ ይችላል ብለው አያምኑም። “ግላዊነት” የሚያጠቃቸው ሰዎች በራሳቸው ላይ ከሚገባው በላይ ትኩረት ስለሚሰጡ እነርሱ ከሚያ ስቡት የበለጠ ሌላ ሰው ማሰብና ማድረግ ይችላል ብለው አያምኑም። “ግላዊነት” የሚያጠቃቸው ሰዎች “ትናንሽ አምላ ኮች” እንደ ሆኑ ስለሚሰማቸው “ይሰገድልኝ” የሚል ዝንባሌ ያጠቃቸዋል። ይሁን እንጂ ሰዎች በውስጣቸው ያለውን ተፈጥሮአዊ ችሎታ ማወቅ በሌላው ሳይደገፉ በራሳቸው ሁለት እግር መቆምና ችሎታቸውን በተግባር ላይ ማዋል ይኖርባቸውል። ሁኔታን ፈጣሪዎች እንጂ ሁኔታ የፈጠራቸው ብቻ መሆን የለባቸውም። ሰው በግሉ እንዳይቆም፣ የራሱን ምርጫና ውሳኔ እንዳያደርግ ከፍተኛ ተጽኖ በማድረግ አስተሳሰቡን ለመቆጣጠርና ለመቀየስ የሚታገሉ ልዩ ልዩ ኃይሎች ያጋጥሙታል። ማስታወቂያዎች ፋታ ሳይሰጡ ቀንና ማታ ዓይኑንና ጆሮውን በመማረክ ጎጂ የሆኑትን ነገሮች እንኳን ሳይቀር እንዲቀምስ ያባብሉታል። ይህን ዓይነት ከባድ ትግልና ተጽእኖ ባለበት ዓለም “እምቢ” ብሎ ግላዊ የሆነ ምርጫና ውሳኔ ይዞ መቆየት ከባድ ነው። በአለንበት ህብረተሰብ ተቀባይነት ኖሮን መቆየት እንድንችል አካባቢያችንን መምሰል አስፋላጊ ቢሆንም “አድር ባይ ጠባይና” “የተገዢነት” ባህሪይ በውስጣችን የሚፈጥር ከሆነ ግን የግል ጠባያችንን ደካማ ያደርገዋል። ይሄም “ግላዊነታችንን” (individuality) ይገፋል። የምናደርገውና የምንወስነው ሁሉ በእኛ ፈቃድና ምርጫ ሳይሆን ሌሎች እንድናደርግ ስለገፉን ብቻ ይሆናል። ለምርጫችን ወሳኞቹ ሌሎች ከሆኑ በራሳችን እምነት እያጣን እንሄዳለን። ስለሆነም ሁልጊዜ የራሳችንን አስተያየት በድፍረት ከመናገራችን በፊት ሌሎች የሚሉትን በቅድሚያ ለመስማት እንፈልጋለን። ከሌሎች የተለየን ሆነን እንዳንገኝ ንግግራችን እንደ “ገደል ማሚቱ” የሌሎችን ድምጽ የሚያስተጋባ ብቻ ይሆናል። በዚህም ጠንካራ የሆነ የራሳችን አቋም እንደሌለን ያሳያል። አስተያየታችንና ስሜታችንን ከመግለጻችን በፊት ከአሸናፊው ጋር ለመተባበር ስንል፥ የትኛው ክፍል አይሎ እንደሚገኝ ለማወቅ ከዳር ሆነን እነመልከታለን።

ዶክተር ጆሴፍ ኒውተን የተባለው ሰው ማንኛውም ሰው በግል ህይወቱ ማድረግ የሚችለው አራት ምርጫ እንዳለው ተናግሯል። ይኸውም፥

1ኛ ከራሱ መሸሽ

2ኛ ሌሎችን መስሎ መኖር ይኸውም “ሌሎች ካደረጉት እኔ እማላደርግበት ምክንያት የለም” ማለት፥

3ኛ የራሱ የሆነ ዓላማና ግብ ይዞ እራሱን ሥነ ሥርዓት (discipline) በማስያዝ ወደፊት እስከ መጨረሻው መጓዝ፥

4ኛ ከእርሱ በላይ ለሆነው ኃይል እራሱን ሰጥቶ ያ ሰው ወይንም ኃይል እንዲመራው ማድረግ ነው። ከነዚህ ከአራት ምርጫዎች የዘመኑ ክርስትያኖች በየትኛው ክፍል ውስጥ ይበልጥ ይገኙ ይሆን? እንደ ሁለተኛው ክፍል መልካቸውንና ቅርጻቸውን እንደ አካባቢው እንደ ሁኔታው የሚለዋውጡ ይበዙ ይሆን? ክርስትያኖች የራሳችን የሆነ አቋም ያለን የራሳችን ምርጫ ያለን፥ በራሳችን አስተያየትና ሚዛን የማናፍር ጠንካራ የሆነ ባህሪ እንዲኖረን ያስፈልጋል። ልዩ ሆኖ መቆም “እሺ” የሚለው ቁጥር በበዛበት አካባቢ “እምቢ” ብሎ ለብቻ መቆም ከፍተኛ ዋጋ ሊያስከፍል ይችላል። ታሪክ ያልረሳቸው ትላልቅ ሰዎች በዙሪያቸው የሚነፍሰውን ኃይለኛ ነፋስና ማዕበል ሳይፈሩ ቀጥ ብለው የቆሙ ናቸው። የራሳቸው የሆነ ግብና ዓላማ እንዲሁም መሠረታዊ አቋም (principle) የነበራቸው ነበሩ። ምንም ያህል ዋጋ ቢያስከፍላ ቸውም የያዙትን ዓላማ አላስለወጣቸውም። እርግጥ ነው በዚሁ ምክንያት ተቃውሞ፣ ነቀፌታ፣ ስደት ደርሶባቸዋል። ይሁን እንጂ ከሚያምኑበት አንዲት ስንዝር እንኳን ፈቀቅ አላሉም። የግል መመሪያውን ያልጣለ፣ የተፈጥሮ ችሎታውን ያለአግባብ ያልሸቃቀጠ፣ ክፉ ከሆነው ጋር ያልተባበረ፣ የአካባቢው ውጤት ሳይሆን ራሱ የሁኔታዎች ፈጣሪ የሆነ ጠንካራ ባህሪ ያለው ሰው ነው።

## አቋማቸውን የለዋወጡ

ሰው አካባቢውን መለወጥ በማይችልበት ወቅት፥ እንደ ጊዜውና እንደ ሁኔታው እራስን አመቻችቶ መኖር “አዋቂነት ነው” የሚባልበት ጊዜ አለ። ይሁን እንጂ በሌላ በኩል የአካባቢውን ሁኔታ መለወጥ ሲቻል ወይንም “አይስማማኝም! እምቢ” ብሎ መቆም በሚቻልበት ወቅት አቋምን ለጊዜያዊ ጥቅም ሲባል መለዋወጥ “ደካማነት” ነው። መጽሐፍ ቅዱስ አንዳንዶቹን ለትምህርታችን ይጠቅሳቸዋል።

1) ዴማስ፥ “ዴማስ ይህን ዓለም ወዶ ትቶኛል” ይላል ጳውሎስ (2ኛ ጢሞ 4፥10)። ዴማስ ዓለም ለምታቀርብለት ግብዣ “እምቢ” ማለት ኃይል ስለአጣ አቋሙን ለወጠ። በዚህም የአገልግሎት ባልደረባው የነበረው ጳውሎስ ልቡ ተሰበረ።

2) የናስ አንጥረኛው እስክንደር፥ ጳውሎስ ልቡ ያዘነው የተጎዳው በዴማስ ብቻ አይደለም። የናስ አንጥረኛው እስክንድርም በጣም ጎድቶታል። እስክንድር ለምን በጳውሎስ ላይ ክፉ መናገር እንደ ጀመረ አናውቅም። የምናውቀው ነገር ቢኖር ጳውሎስ በጣም ያዘነበት መሆኑን ብቻ ነው። ጳውሎስ “የናስ አንጥረኛው እስክንድር ብዙ ክፉ ነገር አደረገብኝ፤ ጌታ እንደ ሥራው ይከፍለዋል። እርሱ እኛ የምንናገረውን በብርቱ ስለ ተቃወመ አንተም ራስህ ከእርሱ ተጠንቀቅ” ሲል ለጢሞቴዎስ ይጽፍለታል (2ጢሞ 4፥14-15)።

3) በጳውሎስ አካባቢ የነበሩ አንዳንድ አማኞች፥ አቋማቸውን በመለዋወጣቸው ጳውሎስ ያዘነባቸው ጥቂቶች እንዳልነበሩ መጽሐፍ ቅዱስ ያመለክተናል። ያገለግላቸው፣ ይረዱኛል፣ ይጠቅሙኛል ብሎ ያሰባቸው አንዳንድ አማኞች ጳውሎስ በችግር ውስጥ ሲሆን ሃሳባቸውን ለውጠው የሸሹት ብዙዎች ነበሩ። በእነርሱም ልቡ በጣም ያዘነ እንደነበረ በሚጽፈው ደብዳቤ ወይንም መልዕክት መረዳት ይቻላል (2ጢሞ 4፥16)።

4) ዲዮትራፌስ፥ አማኝ እንደ ነበረና ለአገልግሎት ጥማት እንደነበረው ግልጽ ነው። መሪ ለመሆን ከፍተኛ ፍላጎት ስለነበረው “መሪነቴን” ይቀናቀኑኛል ብሎ የሚያስባቸውን ወንድሞች ሁሉ እየጠላ መጣ። ዮሐንስ ስለ ዲዮትራፌስ የተናገረውን ከባድ ነገር ስንሰማ ምን ያህል እንደተጎዳ መረዳት ያስችለናል (3 ዮሐንስ 9-10)። መሪ የመሆን ጥማት ያላቸው አንዳንድ “ዲያትራፌሶች” በእኛም ዘመን፣ በእኛም አካባቢ አይጠፉም። የሚያሳዝኑት “ዲዮትራፌሶች” አይደሉም። የሚያሳዝኑት ግን የራሳቸው አቋም የሌላቸው “ከዲዮትራፌሶች” ጋር መስለው የሚኖሩ ናቸው። “ዲዮትራፌሶች” የሚፈጽሙት ተግባር ልክ እንዳናልሆነ በደንብ ያውቃሉ። ግን “ልክ አይደላችሁም፤ ስታችኋል” ለማለት ድፍረት የላቸውም። ይህን ለማለት ፍራቻቸው ከማህበራቸው እንዳያስወጡአቸው ብቻ ነው።

.................................................................................

**በሚቀጥለው ክፍል እስክንገናኝ፥ የጌታ ጸጋና ሰላም ከሁላችን ጋር ይሁን።**